# ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም እና ሦስት ሺህ ዓመታትን ያስቆጠረው ታሪኳ በአጭሩ!



ነዋ በግዑ መስቀል ዘሀሉ በተድባበ ማርያም (ተድባበ ማርያም ብቻ የሚገኘው ነዋ በግዑ መስቀል)

Scanned by CamScanner

# ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም እና ሦስት ሺህ ዓመታትን ያስቆጠረው ታሪኳ!

ነዋ በግዑ መስቀል ዘሀሉ በተድባበ ማርያም (ተድባበ ማርያም ብቻ የሚገኘው ነዋ በግዑ መስቀል)

አዘጋጅ፦ በአውቀቱ ይልማ ዘተድባበ ማርያም፤ ሥልክ ቁጥር (0911906348)

2013 ዓ ም በርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚከበረውን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የልደት በዐል እና 478ኛውን የአፄ ገላወዴዎስ የድል በዐል ምክንያት በማድረግ የበተዘጋጀ!

አሳታሚና አከፋፋይ፦ የርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት፤ (መልአከ ጽዮን አባ ግርማ ከበደ የርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሥልክ ቁጥር፦ 0938045357)



Scanned by CamScanner

ማውጫ ፦

ገጽ


መቅድም........................................................................... 3

ምዕራፍ አንድ

ተድባበ ማርያም በብሉይ ኪዳን.......................................5

ምዕራፍ ሁለት

ተድባበ ማርያም በሐዲስ ኪዳን.......................................11

ምዕራፍ ሦስት

ተደባበ ማርያም ከአሕመድ ግራኝ ወረራ በኋላ.........................16

ምዕራፍ አራት

ከትምህርት መንገድ ፈቀቅ የሚል ሰው በሙታን ጉባዔ ይቀመጣል.......................................................... 22

ምዕራፍ አምስት

ተድባበ ማርያምና ዘመን ተሻጋሪ ቅርሶቿ..................... 28




Scanned by CamScanner

## መቅድም፡-

የርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥርወ መሠረት እና ሦስት ሽህ ዘመናትን ያስቆጠረው ዘመን ተሸጋሪው ታሪኳ የሚጀምረው ከገናናዋ ኢትዮጵያዊት ንግሥት፣ ንግሥተ ሳባ (ንግሥተ አዜብ) ዘመነ መንግሥት ነው። ንግሥተ ሳባ በእሥራኤል ገናና ከነበረው ንጉሥ ሰሎሞን የወለደችውን ቀዳማዊ ምንይልክን ተከትለው የመጡ ሌዋውያንና መሣፍንት ከእሥራኤል ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን ተከትሎ በ982 ዓመተ ዓለም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው፤ የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለችበት ዙሪያውን በገደል ከተከበበ ተራራ ላይ ተድባበ ጽዮን በሚል አሪታዊ ስያሜ የተመሠረተችው። የሀቺ በሦስቱም ሕግጋት ማለትም በሕገ ልቡና፣ በሕገ ኦሪት እና በሕገ ወንጌል እንደ የዘመናቱ ሕግና ሥርዓት አምልኮተ እግዚአብሔር እንደ ተፈጸመባት የሚነገርላት ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርም ከ3,000 ዓመታት በፊት አሁን ካለችበት ተራራ ላይ ስትመሰረት ስሟ ገሊላ ተድባበ ጽዮን ይባል እንደ ነበረ አያሌ ጥንታውያን ጳሐፍት ጽፈዋል፤ ክብረ ነገሥትን ጨምሮ በርካታ ጥንታውያት የታሪክ መጻሕፍትም ዘመን ተሸጋሪውን እና አንጸባራቂውን የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በየዓምዳቸው መዝግበው ይዘዋል።

የርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡-በሦስት ክፍል (ምዕራፍ) ከፍሎ መመለከት ታሪኩን በወጉ ለማጥናት ይረዳል።

ስለሆነም፡-

በምዕራፍ አንድ ተድባበ ማርያም በብሉይ ኪዳን ዘመን፣

በምዕራፍ ሁለት ተድባበ ማርያም በሐዲስ ኪዳን ዘመን እና፣



Scanned by CamScanner

በምዕራፍ ሦስት ተድባበ ማርያም ከአሕመድ ግራኝ ወረራ በኋላ በሚል በሦስት ክፍል (ምዕራፍ) ተዘጋጅቷል።

ሌላው በምዕራፍ አራትና አምስት በገዳሚ ውስጥ ስለሚገኙ ዘመን ተሻጋሪ ቅረሶች በክፊል እና በቅርቡ የግንባታ ሥራው ስለሚጀመረው ጥንታዊው የአባ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የድጓ ምስክር ት/ቤት፤የካህናት ማሰልጠኛና አጠቃላይ አዳሪ የአብነት ትምህርት ቤት በተመለከተ አጠር ያለ ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል። በመጨረሻም ይህ ጽሑፍ የተዘጀው አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኗን ታሪክና በውስጧ የሚገኙትን መንፈሳዊና ባህላዊ ቅረሶቿን በተመለከተ የደብሩ ሰበካ ጉባዔ በመጽሐፍ መልክ ለማሳተም ስለ ተዘጋጀ የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ታሪክ የያዘው መጽሐፍ እስከሚታተም ድረስ ለዋናው መጽሐፍ መዳረሻ ይሆን ዘንድ ታሳቢ ተድርጎ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።



Scanned by CamScanner

## ምራፍ አንድ

## ተድባበ ማርያም በብሉይ ኪዳን፡-

በቀደመው ስሟ ገሊላ ተድባበ ጽዮን ተብላ የምትታወቀው ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም የምትገኘው በደቡብ ወሎ (በቀድሞው ቤተ አምሐራ ሣይንት) ከወረዳው ዋና ከተማ አጅባር 28 ኪሎ ሜትር ርቀት፣ ዙሪያውን በገደል በተከበበና አሥራ ሁለት መውጫና መግቢያ የተፈጥሮ በሮች ባሉት አምባ ላይ ነው።

አማራ ሣይንትን በተመለከተ አንዳንድ የታሪክ ምሁራን የአማራ ሣይንት ትክክለኛ ስሙ አምሐራ ሣይንት ሳይሆን አምሓራ ሠዬምት ነው ይላሉ። አምሐራ ሠዬምት የሚለው ሥያሜ የግዕዝ ቃል ሲሆን በአማርኛ የአማራ ሹሞች እንደ ማለት ነው። አካባቢው ይህን ስያሜ ያገኘው ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት፣ ልዑላንና ልዑላት፤ መሳፍንትና መኳንንት የዘር ኃረጋቸው የሚመዘዘው ከዚህ አካባቢ ስለሆነና አገር ለማቅናትና ጠላት ለማጥፋት መላ ኢትዮጵያን ዙረው አዳርሰው ያመነውን አስገብረው ያላመነውን ቀጥተው ሲመለሱ የዕረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ዙሮ መግቢያ ቤታቸው ስለሆነ አካባቢው በነገሥታቱ፣ በልዑላኑና በልዑላቱ ስም አምሐራራ ሠዬምት ተብሎ ተሠይሟል፤ ይላሉ ቀደምት የታሪክ ምሁራን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት። ‹‹በስመ ኃዳሪ ይዬዋዕ ማኃደር›› [በአዳሪው (በባለ ቤቱ) ስም ማደሪያው (ቤቱ) ይጠራል]፤ በሚለው ብሂል የተሰጠ ስያሜ ይመስላል። እንደ ሊቃውንቱ ገለጻ ከሆነ ሣይንት የተባለው በጊዜ ሂደት የፊደል ተፋልሶ ስላጋጠመው እንጂ ትክክለኛ ስሙ አምሐራ ሠዬምት ነው።

አማራ ሣይንትን አሁን ባለው የአስተዳደር ወሰን በምዕራብ የምሥራቅ ጎጃም ዞን ሞጣ ወረዳና የደቡብ ጎንደር ስማዳ ወረዳዎች፤



Scanned by CamScanner

በሰሜንና በምሥራቅ የመቅደላ ወረዳ፣ በደቡብ የደብረ ሲና ወረዳ (ቦረና መካነ ሰላም) ያዋስኗታል።

ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ከአማራ ሣይንት ወረደ ዋና ከተማ አጅባር በስተ ሰሜን በኩል በቅርብ እርቀት ላይ ትገኛለች። ተድባበ ማርያምን አሪታዊ ስያሜ ያላቸው የታቦር ተራራ፣ደብረ ዘይትና ኮሬብ የተባሉ አካባቢዎችም የሚያዋስኗት ሲሆን የምትገኝበት ቦታ ዙሪያው በጥርብ ዓለት ገደል የታጠረ ሆኖ 12 የተፈጥሮ መግቢያና መወጫ በሮች ብቻ አሏት።

የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያ በሥሯ የምታስተዳድራቸው ሌሎች ዘጠኝ አብያተ ክርስቲያናትም በዙሪያዋ አሉ። አምባው ገኸ መሬት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ተፈጥሮ የቸረው ከፍተኛ ውበት አለው።

ወደ ሥርወ ታሪኩ ስንመለስ የርዕሰ አድባራትቲ ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲየን በኢትዮጵያ መስዋዕተ ኦሪትቲ ከተሰዋባውና መናብርተ ጽዮን በመባል ከሚታወቁት አራትቲጥንታውት አብያተ ክርስቲያናት ማለትም

ሀ. አክሱም ጽዮን፣

ለ. ተድባበ ጽዮን፣

ሐ. መርጡለ ማርያምና፣

መ. ጣና ቂርቆስ (ጽርሐ ጽዮን) መካከል አንዷ እንደ ሆነችና በአመሠራረት ቅደም ተከተልም ከአክሱም ጽዮን ቀጥላ በሁለተኛነትቲየምትገኝ ጥንዊትና ብቸኛ ባለታሪክ ቤተ ክርስቲያን ናት።ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም በ10ቸው መቶ ክፍለ ዘመን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ማለትም በ982 ዓመተ ዓለም አሁን ካለችበ ቦታ ላይ ተመሥርታለች። የተመሠረተችውም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪትን ለማስፋፋት ከመጡቲ ነገደ እስራኤላውያን መካከል አንዱ በሆነው በሊቀ ካህኑ



Scanned by CamScanner

አዛርያስ እና በመሥፍኑ ሣቤቅ መሆኑን የቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ያስረዳል።

ሣቤቅ በመባል የሚታወቀው እሥራኤላዊ መሥፍን የንጉሥ ዳዊት ወንድም የአሚናዳብ የበኩር ልጅ ሲሆን ከቀዳማዊ ምንይልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ አብሮ የመጣ መሥፍን መሆኑ ይታወቃል። የተድባበ ማርያም የመጀመሪያ መጠሪያዋም ገሊላ ተድባበ ጽዮን ይባል እንደ ነበረ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ተድባበ የሚለው ቃል ከግዕዝ የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ድባብ ወይም ጫፍ እንደ ማለት ነው። በክብረ ነገሥት መጽሐፍእእንደ ተገለጸው አዛርያስ፣ ሳዶቅ የተባለውእእሥስራኤላዊ ሊቀ ካህን ልጅ ሲሆን ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ነገደ እአሥራኤላውያንንእእንዲመራ በንጉሥ ሰለሞን ታዝዞ የመጣ እና ሕገ ኦሪትን በኢትዮጵያ ከመሠረቱት እና ካስፋፉት ካህናት መካከል አንዱ ነዉ።እንደ ክብረ ነገሥት ገለጻ ከኦሪት (ከብሉይ ኪዳን) ጀምሮእእስከ ሐዲስ ኪዳን (የክርስትና እምነት) በኢትዮጵያ እስከ ተሰበከበት ዘመን ድረስ ብሉይ ኪዳን ማለትም ሕገ ኦሪትን የመሠረቱና ያስፋፉ ከቀዳማዊ ምንይልክ ጋር የመጡ ሌዋውያን ከህናት ናቸው። በሐዲስ ኪዳንም የክርስትና ሃይማኖትን እንዲስፋፋ ከደረጉት ዋና ዋና ካህትና መምህራን መካከል አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን መምህራን የሊቀ ካህናት አዛርያስ ዘሮች ናቸው።

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው በ982 ዓመተ ዓለም ቀዳማዊ ምኒልክ ከአባቱ ከንጉስ ሰሎሞን መንግሥት ተቀብሎ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ 4 መናብርተ ጽዮን ይዞ መጥቷል።

ቀዳማዊ ምንይልክ 4ቱን መናብርትና መንግሥትን ከአባቱ ሰለሞን ተቀብሎ ሲመጣ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ 12,000 መሣፍንትና መኳንንት ወይዛዝርት 1,500 በተግባረ እድ የሰለጠኑ የወርቅና የብረት፣ የመዳብ፣ የበረትና የነሐስ አንጥረኞች፣ አዋቂዎች፣ ጠቢባን፣ ጸረብተ



Scanned by CamScanner

ዕፀውና ወቀረተ አዕባን ናቸው። እነዚህ ኢትዮጵያ ገብተው በየክፍለ ሀገሩ ሥራ ሲጀምሩ የተወሰኑት አክሱም ከተማ ቀርተዋል። የዳዊት ወንድም ልጅ ማለትም የአሚናድብ ልጅ መሥፈኑ ሣቤቅ ከሊቀ ካህናት አዛርያስ ጋር ተከዜን ተሻግሮ ከአሁኑ አምሐራ ሳይንት ደረሰ። ከዚያም ዙሪያዋን በገደል የተከበበችና አሥራ ሁለት በሮች ያሏት አምባ ላይ ደርሶ ደብተራ ኦሪት ሠራ። የአምባዋንም ስም የአባታችንን የዳዊት ከተማ ደብረ ጽዮንን ትመስላለች ሲል በሀገሩ ሰም ገሊላ፣ ተድባበ ጽዮን ብሎ ሰየማት፤ ሊቀ ካህናት አዛሪያስም ስሟን በቡራኬ አጸደቀለት።ከዚያም በተድባበ ጽዮን አቅራቢያ ያሉ አካባቢዎችን አሻግሮ እያየ በሀገሩ (በኢያሩሳሌም አቅራቢያ ባሉ በታዎች) ምሳሌ፡- ደብረ ዘይት፣ ኬብሮን፣ እያሪኮ፣ ኢየሩሳሌም፣ ሎዛ፣ ደብረ ታቦር አያለ በዙሪያዋ ያሉትን ቦታዎች ሁሉ አዲስ ስያሜ ሰጣቸው። እነዚህ ቦታዎች አሁንም ድረስ በዚሁ ሰም ነው የሚጠሩት። በተለይ የታቦር ተራራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ድርሻ ያለው ታሪካዊ ተራራ ነው። በታቦር ተራራ ላይ አፄ ይኩኖ አምላክ ነግሠበታል፤ አማርኛ ቋንቋ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ታውጆበታል። በኋላም በአጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የቅኔ ፈጣሪዎቹ እነ ዮሐንስ ገብላዊና ሠምረ አብ ወልደ ገብርኤል በቅኔ የተራቀቁበት ታሪካዊ ተራራ ነው። ሌሎችም ሊባኖስ፣ ደማስቆ፣ አርሞንኤም፣ ደበር ፋራን፣ ተብለው የተሰየሙ ኦሪታዉያን ቦታዎች አሉ። በተለይ ሊባኖስ የተባለው አገር ከቦረና ዋና ከተማ መካነ ሰላም በቅርብ ርቀት የሚገኝ ሲሆን ለሊቀ ካህናት አዛርያስ እርሰተ ጉልት ሁኖ የተሰጠ ስንዴና ገብስ የሚመረትበት ለም መሬት ነበር።

በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት እንደ ደብተራ ኦሪት (ምኩራብ) ሁና ከ982 ዓመተ ዓለም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እስከ 330 ዓመተ ምሕረት ድረስ ለ1312 ዓመታት ያህል መስዋዕተ ኦሪት የተሰዋባት ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ጌታችንና መድኃኒታችን



Scanned by CamScanner

ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ዓመት ፍዳ ዓመተ ኩነኔ በዓመተ ምሕረት፣ ብሉይ ከዳን በሓዲስ ኪዳን፣ መስዋዕተ ኦሪት በአማናዊው የኢሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እስከሚተካ ድረስ ስሟ ገሊላ ተድባበ ጽዮን፣ እየተባለ 1312 ዓመታት በኦሪቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት በሊቀ ካህናት ነበር ትመራ የነበረው። ከ330 ዓ ም በኋላ ግን በቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ እና በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ) ትእዛዝ ተድባበ ጽዮን በመባል ይታወቅ የነበረው ኦሪታዊ ስሟ ተቀይሮ አማናዊት ጽዮን በሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ስም ተድባበ ማርያም ተብሎ ተሰይሟል። ሊቀ ካህናት ይባል የነበረው የአስተዳዳሪዋ ስመ ማዕረግም በትረ ያርክ ተብሏል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሦስቱም ሕግጋት (ሕገ ልቡና፣ ሕገ ኦሪትና ሐዲስ ኪዳን) በየተራ የተፈጸሙበት ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗን በአገር ቤትም ሆነ በውጪው ዓለም ያሉ የታሪክ ተመራማሪዎች በአንድ ድምፅ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። ስለሆነም በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ መስዋዕተ ኦሪት የተሰዋባቸው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ይታወቃል። ለምሳሌ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ብርብር ማርያም ገዳም፣ በሰሜኑ እንደ ኃዪላ ሚካኤል ያሉ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ሌሎችም መስዋዕተ ኦሪት የተሰዋባቸው አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ይነገራል። ነገር ግን መናብርተ ጽዮን የሚባሉት አራቱ ማለትም፡- አክሱም ጽዮን፤ ተድባበ ማርያም፤ መርጡለ ማርያምና ጣና ቂርቆስ ብቻ ናቸው።

እነዚህ መናብርተ ጽዮን በመባል የሚተወቁት አራቱ ጥንታውያን (ኦሪታውያን) ገዳማትና አድባራት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ሥርዓተ ንግሥ የሚገኙና ሥርዓተ ንግሡን በቀጥታ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ ናቸው።



Scanned by CamScanner

በዚህ መሠረት፡- ከቀዳማዊ ምንይልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ አጤ ኃይለ ሥላሴ ድረስ እነዚህ አራት መናብረት በአንድ ሁነው መክርው ኢትዮጵያን በንጉሠ ነገሥት የሚመራ ንጉሠ ነገሥት ቀብተው እያነገሡና ሥርዓተ ንግሥናውን እየመሩ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ዘልቀዋል።

በሥርዓተ ንግሥ ጊዜ የአራቱ መናብርተ ጽዮን ተግባርና ኃላፊነት፡-

1. የአክሱም ጽዮን ንቡረ ዕድ፡-

የአክሱሙ ንቡረ ዕድ ከቀዳማዊ ምንይልክ ጀምሮ ሲወርድ ሲወራረድ በመጣው ሥርአት መሠረት ማናቸውም ንጉሥ ሲነግሥ በሥርዓተ ንግሥ ጊዜ ዘውዱን በንጉሠ ነገሥቱ እራስ ላይ በክብር ያቀዳጃል፡፡

2. የተድባበ ማርያም በትረ ያርክ፡-

የተድባበ ማርያሙ በትረ ያርክ በሥርዓተ ንግሡ ላይ ቅንት፣ ሰይፈከ፣ ኃያል፣ ውስተ፣ ሐቋከ፡፡ ብሎ ሰይፍ መንግስቱን ለንጉሡ ያስታጥቀዋል በትረ መንግስቱን ሕለት ወርቁን ጠላተህን በእጅህ ጭብት በእግርህ እርግጥ አድርገህ ግዛ ብሎ በቀኝ እጁ ያስይዘዋል፡፡ በ1923 ዓ ም አጤ ኃይለ ሥላሴ ሲነግሡ በሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ሥርዓተ ንግሡን በዚህ መሠረት የፈጸሙት የተድባበ ማርያሙ በትረ ያርክ፣ በትረ ያርክ አፈ ወርቅ ናቸው።

3. የመርጡለ ማርያም ርዕሰ ርኡሳን፡-

የመርጡለ ማርያሙ ርዑሰ ርዑሳን ልብሰ መንግሥቱን ያለብሰዋል፡፡

4. የጣና ቂርቆስ ሊቀ ካህናት፡-

የጣና ቂርቆሱ ሊቀ ካህናት ቅብዓ መንግስቱን ይቀባዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሥረዓተ ንግሥ የሚፈጸመው ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን የተውጣጣው ጸሎት ከተፈጸመ በኋላ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

በእነዚህ አራት መናብርተ ጽዮን ያልነገሠ ንጉሥ ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ በተዋሕዶ ሃይማኖት ፀንቶ ሊኖር አይችልም። እነዚህ ባሉበት ከነገሠ ግን ሀገር ለመጠበቅ ሁሉን ነገር ለማድረግ ይችላል፡፡ ይሄውም ከቀዳማዊ ሚኒሊክ ሲያያዝ መጥቶ እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ በመናብርተ ጽዮን ነግሠዋል፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ሁኔታ ነግሰው 43 ዓመታት ገዝተው አልፈዋል፤ ታሪካቸው ግን ይቀጥላል።

## ምዕራፍ ሁለት

## ተድባበ ማርያም በሐዲስ ኪዳን

ከ10 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (982 ዓመተ ዓለም ቅ.ል ክ) እስከ 330 ዓ.ም ማለትም ከቀዳማዊ ምንይልክ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ለ1312 ዓመታት ደብተራ ኦሪት ሁና መስዋዕተ ኦሪት እየተሰዋባት የቆየችው ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም በ330 ዓ.ም ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኗን በአዲስ መልክ እንፀው ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል፣ ከብሉ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን ሕግ አሸጋግረዋታል፡፡

ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ ከአክሱም ጽዮን ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ያነፁትን የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሠርተው እንዳጠናቀቁ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሰ) ቤተ ምኵራብን በቤተ መቅደስ፣ ሕገ ኦሪትን በሕገ በወንጌል ቀይረዋል፡፡ በቤተ መቅደሷም በመስዋዕተ ኦሪት ፈንታ



Scanned by CamScanner

በሐዲስ ኪዳን ሕግ መሠረት አማናዊው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንዲሰዋ አድርገዋል። ስሟንም ተድባበ ማርያም ብለው አማናዊት ጽዮን በሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ስም ሰይመዋታል። በመቀጠልም ለ1312 ዓመታት የደብተራ ኦሪቱ መሪ ስመ ማዕረግ ሆኖ የቆየውን ሊቀ ካህናት የሚለውን ስመ ማዕረግ በሐዲስ ኪዳን (በመንፈሳዊው ዘርፍ) ትልቁና የመጨረሻ ደረጃ በሆነው በትረ ያርክ በሚልው ስመ ማዕረግ ተክተው የቤተ ክርስቲያኗን መሪ ብትረ ያርክ አድርገው ሹመውታል። ገድለ አብርሃ ወአጽብሐ ስለ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከሚተርከው ታሪክ መካከል የሚከተለው አንቀጽ በጉልህ ተጽፎ ይገኛል። ‹‹ወአደዉ ፈለገ ተከዚ ወቦኡ ብሔረ አምሐራ ወሐነፁ በህየ መቅደሰ ወሠመይዋ ለይእቲ መቅደስ ተድባበ ማርያም። ወሤሙ በውስቴታ በትረ ያርክ ዝ ውእቱ ሊቀ ካህናት ወዓልዓሉ ክብራ እምኵሉን አድባራት›› ትርጉም፦ የተከዚን ወንዝ ተሸግረው አማራ አገር ደረሱ።በዚያም ቤተ መቅደስን ሠሩ ይህቺንም ቤተ መቅደስ ተድባበ ማርያም ብለው ሠየሟት። በውስጧም በትረ ያርክ ሾሙ በትረ ያርክ ማልት ሊቀ ካህናት ማልት ነው። ክብሯም ከአድባራት ሁሉ በላይ እንዲሆን አደረጉ ይላል።ክብሯም ከሌሎች አድባራት ሁሉ በላይ እንዲሆን አደረጉ ማለቱ በመንፈሳዊው ዘርፍ ትልቁና የመጨረሻ ደረጃ የሆነውን በትረ ያርክ የሚልውን ስመ ማዕረግ ለተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰጥተው የቤተ ክርስቲያኗን የበላይ ኃላፊ ወይም መሪ ብትረ ያርክ ብለው መሾማቸውን እና በውስጧ የሠሯቸው ሥርዓታት ከሌሎች አድባራትና ገዳማት ልዩ መሆናቸውን ሲያጠይቅ ነው። በሊቀ ጳጳሱ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና በአብርሃ ወአጽብሐ ለተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በትረ ያርክ ሁኖ የተሾመው የመጀመሪያው በትረ ያርክ፣ በትረ ያርክ መርሐ ጽዮን በመባል ይታወቃል። በትረ ያርክ መርሐ ጽዮን የተድባበ ማርያም በትረ ያርክ ሁኖ የተሾመው በ 330 ዓ ም ነው።በዚህ መሠረት ከአብርሃ ወአጽብሐ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ



Scanned by CamScanner

ዘመነ መንግሥት ድረስ ብዙ በትረ ያርኮች በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተሾሙ አገልግለው አረፍተ ዘመን እየገታቸው አልፈዋል፡፡ የመጀመሪያውና በአብርሃ ወአጽብሐ ዘምን ተሾሞ የተድባበ ማርያም በትረ ያርክ የነበረው በትረ ያርክ መርሐ ጽዮን ሲሆን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ነበሩትና የመጨረሻው የተድባበ ማርያም በትረ ያርክ፣ በትረ ያርክ ወልደ ገብርኤል በመባል ይታወቃሉ፡፡

አብርሃ ወአጽብሐ የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን እጅግ ባማረና ውብ በሆነ ግብረ ሕንፃ አንፀውና ሠርተው ካጠናቀቁ በኋላ ባነፁት ቤተ ወቅደስ እግዚአብሔር እንዲመሰገንበትና መንፈሳዊ አገልግሎቱ ዓመቱን ሙሉ ያለማቋረጥ እንዲደረስ ሥርዓት ሠርተዋል፡፡ ይህንንም ሥርዓት የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ 999 የሚሆኑ ካህናትን የነግሀ፣ የሠለስት፣የቀትር፣ የተስዓቱ ሰዐትና የሠርክ እንዲሁም የምሴት ብለው መድበዋል፡፡

ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ የተድባበ ማርያምን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አንፀው ሲፈጽሙ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በእመቤታችን ስም የታነፀውን ቤተ ክርስቲያን በሜሮን አክብረው ቅዳሴ ቤተ ክርስቲኑን አክብረዋል፡፡ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቅዳሴ ቤቷን ሲያከበሩ የቀደሱበት በአረማይክ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፈ ቅዳሴና የእጅ መስቀላቸው በአሁኑ ሰዐት በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀመጦ ይገኛል፡፡ ሌላው በቅርስነት ተመዝግቦና በክብር ተቀምጦ የሚገኘው አባ ሰላማ ቅዳሴ ቤክርስቲኗን ያከበሩበት ተአምራዊው ቅብዐ ሜሮኑ ነው፡፡ አሁን በተድባበ ማርም ቤተ ክርስቲያን በቅርስነት ተመዝግቦ የሚገኘው ይህ ታሪካዊና ተአምራዊ ቅብዐ ሜሮን፣ ሠለስቱ ምዕት በኒቅያ ጉባዔ አድረገው አርዮስን ተከራክረው፣ ረትተው እና አውግዘው ከለዩ በኋላ ወደየ አህጉረ ስብከታቸው ከመለያየታቸው በፊት የጸለዩበት ታሪካዊና ተአምራዊ ቅዱስ ቅብዕ ነው፡፡ አሁን ተድባበ ማርያም ያለው ቅብዐ ሜሮን አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን



Scanned by CamScanner

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሾመው ወደ ሀገረ ስብከታቸው ( ኢትዮጵያ) ሲመጡ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የተሰጣቸው ነው። ስለሆነም ፐትርክናውና ቅብዐ ሜሮኑ አይለያዩምና አባ ሰላማ ቅብዐ ሜሮኑን ከፐትርክናው ጋር ተድባበ ማርያም ነበር የስቀመጡት። ቅብዐ ሜሮኑ እስከ አሁን ድረስ በቦታው አለ፤ ፐትርክናው ግን ያለ ሕግ ተወስዶ ለተድባበ ማርያም ተመጣጣኝ ስያሜ እንኳን ሳይሰጣት እንደ ቀልድ 60 ዓመታት አለፉ፡፡ ይህ ዘይቄድስ ኲሉ በመባል የሚታወቀው ታሪካዊና ተአምራዊ ቅብዐ ሜሮን በነሐስ ማሠሮ (ገንቦ) ሆኖ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጦ እስከ አሁን አለ። ይህን በተመለከተ የሰቆቃወ ድንግል ደራሲ አባ ጽጌ ድንግል፣ አባ ገብረ ማርያም ናቸው የሚሉም አሉ፡-

‹‹ኀበ ኃፀበት በማይ አልባሲሁ ወዐባሉ፡፡

ለሕፃን ድንግል ዝኩ ሰሎሜ ዘተኃዝሉ፡፡

በለሳን ኮነ ሐፈ ሥጋሁ በቈሉ፡፡

ሜሮን ቅብዕ ዘየቄድስ ኩሉ፡፡

ለትእምርት በኃቤነ እስከ ዮም ሀሉ››፡፡

ትርጉም፡- የምታዝለው ሰሎሜ የድንግል ማርያምን ልጅ፤

ልብስና አካል በውኃ ካጠበች ዘንድ፤

እጣቢው በቅሉ ዘይት ሆነ፤

ሁሉን የሚያከብር ቅብዐ ሜሮንም ሁኖ፤

ለምልክት ያህል እስከ ዛሬ ድረስ በኛ ዘንድ አለ፡፡

ሲሉ ደራሲው ሰቆቃወ ድንግል በተሰኘው ድርሰታቸው ጠቅሰውታል። ደራሲው ፡-ለምልክት ያህል እስከ ዛሬ በኛ ዘንድ ዘንድ አለ፤



Scanned by CamScanner

ማለታቸው ይህን ድረሰት ሲደርሱ ተድባበ ማርያም አካባቢ እንደነበሩ ፍንጭ ይሰጣል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ፣ የሆኑት አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ንዋያተ ክህነት የሆኑትን ማለትም የቀደሱበትን መጽሐፈ ቅዳሴያቸውን፣ የባረኩበትን የእጅ መስቀላቸውን እና ቤተ መቅደሱን ቀብተው የከበሩበትን ቅብዐ ሜሮን ከፐትርክናው ጋር አንድ ላይ ተድባበ ማርያም ነው ያስቀመጡት ወይም ለድባበ ማርያም ነው የሰጡት። መጽሐፈ ቅዳሴያቸው (በአረማይክ ቋንቋ የተጻፈ)፣ የእጅ መስቀላቸው እና ቅብዐ ሜሩኑ) እስከ አሁንም ድረስ በቦታቸው በክብር ተቀምጠው ሲገኙ ፐትርክናው ግን አሳማኝ ባልሆን ሁኔታ ከተድባበ ማርያም ተወስዷል። አብርሃ ወአጽብሐ ያነፁት የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲን በመናኙና ደገኛው ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ካሌብ ዘመን እድስት ተደርጎለታል። አፄ ካሌብ የናግራንን ክርስቲያኖች ከአይሁድ ጭፍጨፋ ለመታደግ ወደ የመን ሲዘምቱ የተድባበ ማርያሙ በትረ ያርክ ዘሙሴ ከንጉሡ ጋር አብረው ዘምተዋል። አፄ ካሌብ ለሰማዕታት ናግራን መታሰቢያ አድርገው በሕይወት ያሉትን ክርስቲያኖች አፅናንተው ሲመለሱ በትረ ያርክ ዘሙሴ ግን በዚያው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ደርሰው እንደመጡ ታሪካቸው ያስረዳል። አፄ ካሌብ ከናግራን መልስ አብርሃ ወአጽብሐ የሠሩትን የተድባበ ማርያምን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አድሰዋል። በኋላም አንበሳ ውድም የተባለው ንጉሥ የተድባበ ማርያምን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አድሷል። አንበሣ ውድም ተድባበ ማርያምን አድሶ ሲመለስ ሎዛ ጊዮርጊስን ሠርቶ ነው የሄደው። ሎዛ ጊዮርጊስ የሚባለው ቤተ ክርስቲያን የታነፀበት ቦታ የተድባበ ማርያም ቄሰ ገበዝ ርስት እንደበረ ይነገራል።

የተድባበ ማርያም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በሦስቱ ነገሥታት ማለትም በአብርሃ ወአጽብሐ፣ በአፄ ካሌብ እና በአንበሣ ውድም ዘመነ መንግሥት ዕድሳት ተደረጎለታል። ውስጣዊ ሥርዓቱ ወይም

አስተዳደራዊ መዋቅሩ ግን ምንም ሳይጨመርበትና ሳይቀነስ እስከ አፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ደረሷል፡፡ አፄ ገላውዴዎስም በዘመነ መንግሥታቸው ዋና ከተማቸውን ተድባበ ማርያም ላይ አድርገው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኗን በአዲስ መልክ ዐንፀዋል፤ ሥርዓተ ደብሯንም አብርሃ ወአጽብሐ በሠሩት ሥርዓት ላይ ማሻሻያ አድርገዋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ተድባበ ማርያም ከአሕመድ ግራኝ ወረራ በኋላ

ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት አፄ ብነ ድንግል ሕዝባቸውንና መንግሥታቸውን ለማጥፋት እና አበሻን ቅኝ ለመግዛት በተነሣ በቱርክና ዐረብ ወራሪ እና የምሥራቅ አጥቂ ሲፈተኑ የሰጡት የትእዛዝ ቃል ይህ ነበር፡፡ የጦር መኮንኖቻቸው ለአፄ ልብነ ድንግል እንዲህ አሏቸው፤ ‹‹ወራሪው ኃይል በርትቶ ሁሉን አጣን፤ ምን እናድርግ?›› አፄ ልብነ ድንግልም የመጨረሻውን የጦር ትእዛዝ እንዲህ ብለው ሰጡ ‹‹ወደ አባቶቻችንና አያቶቻችን ወደ አምሐራ ነገሥታት ምድር እናምራ፡፡ አምሐራን እስከ ሞት እንከላከል ዘንድ ወደ አምሐራ በሮች ሄደንና ታግለን እንሙት!›› አፄ ልብነ ድንግል መመሪያውን ለጦር መሪዎቻቸው አስተላልፈው አሁን ኤረር ከሚባለው አካባቢ በካን ከሚባለው ቤተ መንግሥታቸው ተነሥተው፣ሸዋን ለቅቀው እና ሞፈር ውኃን ተሸግረው መካነ ሥላሴ ደረሱ፡፡ ከዚያም የግራኝ አህመድ ጦር እየገፋ ሲመጣ ከአሁኑ አማራ ሣይንት ገብተው የመጨረሻ ያሉትን ምሽግ ሠርተው የሞት ሽረት ትግል አደረጉ፡፡ አማራ ሣይንት ውስጥ ምሽግ ይዘው የግራኝ አሕመድን ጦር መክተው የመለሱበት ቦታ በአሁኑ ሰዐት ዎናግ ተራራ በመባል ይታወቃል፡፡ ዎናግ ሰገድ ማለት የአፄ ልብነ ድንግል የመንግሥት ስማቸው ነው፡፡ አፄ ልብነ ድንግል ፊቅጦር፣ ሚናስ፣ ገላውዴዎስ እና ያዕቆብ የተባሉ አራት ወንዶች



Scanned by CamScanner

ልጆችና ሌሎች ሴቶች ልጆች ነበሯቸው። ፊቅጦር ከግራኝ አሕመድ ጋር በነበረው ጦርነት ተሰውቷል፤ ሚናስ በምርኮ ተይዟል። ያዕቆብ ሸዋ ከዘመድ ጋር ሲቀር ገላውዴዎስ ከአፄ ልብነ ድንግል ጋር አብሮ ከአንዱ ወደ ሌላው አገር ሲንከራተት ከቆየ በኋላ አፄ ልብነ ድንግል ወደ ደብረ ዳሞ ሲሄዱ እና በዚው አረፍተ ዘመን ሲገታቸው ያን ጊዜ ገላውዴዎስ ግራኝን በመልሶ ማጥቃት ለመግጠምና ሠራዊቱን ለማደራጀት ተድባበ ማርያም ገብቶ ተቀምጧል። ተድባበ ማርያምና አፄ ገላውዴዎስ ያን ጊዜ ነው የሚተዋወቁት።

በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ግራኝ አሕመድ የተባለ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነሥቶ በዓረብና ቱርክ እየታገዘ መላ ኢትዮጵያን በመውረር ታሪካዊውን የአፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት አቃጥሎ ከተማቸውንና ነባሩን የኢትዮጵያ ታሪክ ከመሠረቱ ንዶ እንዳልነበረ አድርጎታል። ይልቁንም አብያተ ክርስቲያናት፣ ሊቃውንትና ንዋዬ ቅድሳት ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል፤ ታላቁን ገዳም ደብረ ሊባኖስን ጨምሮ እጅግ በርካታ ጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናትን ከነ መጻሕፍቶቻቸውና ኪነ ሕንፃቸው ጭምር አጥፍቷል።ከታላቋ አክሱም ጽዮን ጀምሮ እስከ ጥንታዊው ጣና ቂርቆስ፣ መካነ ነገሥት ግሸን ደብረ ከርቤ እና እጅግ ውብ በሆነ ኪነ ሕንፃ የታነፁትን እነ ደብረ ነጎድጓድን፣መካነ ሥላሴን፣ ደበር እግዚአብሔር፣ የአፄ በአደ ማርያሟ አትሮንሰ ማርያምን፣ ሐይቅ አባ ኢየሱስ ሞዐ ገዳምን እና የበርካታ ሊቃውንትና የእውቀት ምንጭ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን በእሳት አቃጥሎ እንዳልነበሩ አድረጓቸዋል።

አማራ ሣይንት ግን አፄ ልብነ ድንግል ለጦር መሪዎቻቸው ያስተላለፉትን የጦር መመሪያ ተቀብለው የጦር መሪዎቹ የአማራ ሣይንትን በሮች ዘግተው በመከላከላቸውና የአማራ ሣይንት መልክዐ ምድርም አግዟቸው የግራኝ አሕመድን ጦር በመልሶ ማጥቃት ክፉኛ



Scanned by CamScanner

ስለመቱት የግራኝ ጦር የአማራ ሣይንትን መሬት እግሩ አልረገጠም። በዚህም ምክንያት ተድባበ ማርያምን ጨምሮ አማራ ሣይንት ወስጥ የነበሩ ጥንታውያት አድባራትና ገዳማት ምንም አይነት ጥቃት አልደረሰባቸውም። ለምሳሌ ከግራኝ አሕመድ ወራረ በፊት የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲናት፦

- ጽረሐ አርያም ኦፍ አምጪ ማርያም በአፄ ገብረ መስቀል ቀዳማዊ፣
- ሎዘ ጊዮርጊስ በአንበሣ ውድም የተመሠረተ፣ አንበሣ ውድም ሎዛ ጊዮርጊስን የመሠረቱት ተድባበ ማርያም ደርሰው ሲመለሱ ነው።
- በተለምዶ የገዛዛ ማርያም በመባል የምትታወቀው ጋዛ ማርያም፣ የገዛዛ (ጋዛ ማርያም) በአክሱም ዘመነ መንግሥት እንደተመሠረተች ነው የሚነገረው፤ ከእስክንድርያ ለሚመጡ ጳጳሳት መንበረ ጵጵስና ሁና አገልግላለች። የገዛዛ ማርያም የአራት ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳት መካነ መቃብር መገኛ ናት። አቡነ ተክለ ሃይማኖት (የፀጋ ዘአብና የእግዚእ ኃረያ ልጅ) ዲቁና የተቀበሉት የገዛዛ ማርያም ከአቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ መሆኑን ገድላቸው ይናገራል። የአቡነ ቄርሎስ የእጅ መስቀል በአሁኑ ሰዐት በቅርስነት ተመዝገቦ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጦ የገኛል።
- ወገዴ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሚባሉ ጥንታውያን ገዳማት፣ አድባራትና ሌሎችም በጊዜው አማራ ሣይንት ውስጥ የነበሩ በረካታ አብያተ ክርስቲያናት የግራኝ አሕመድ ጥፍት አልደረሰባቸውም። ምክንያቱም ግራኝ አሕመድ አማራ ሣይንት ውስጥ አልገባምና ነው። በዚህ ምክንያት ጥንት መስዋዕተ ኦሪት የተሰዋባት፣ በኋላም ከአራቱ መናብርተ ጽዮን መካከል ሁለተኛዋና መንበረ በትረ ያርክ፣ የሁሉም ገዳማትና አድባራት እናት የሆነችው ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያምን አፄ ገላውዴዎስ አምባ መጠጊያ፣ ቤተ ጸሎት ትሆናቸው



Scanned by CamScanner

ዘንድ መርጠዋታል። በትረ ያርክ አፈወ ድንግልም ከግራኝ ጦር አምልጠው በመሸሸ ከየአቅጣቻው ወደ ተድባበ ማርያም የሚመጦትን ሊቃውትና ካህናት እየተቀበሉና አፄ ገላውዴዎስንም በጸሎትና በሱባዔ እንዲሁም በምክር ያግዙ ነበር። ከሞትና ከምርኮ የተረፉ መሣፍንትና መኮንንነቱም ግራኝን ድል እስከሚያደርጉ ድረስ ማዕከላቸውን ተድባበ ማርያም ላይ አድርገው በጦርነትና በስደት የተዳከመ ኃይላቸውን እንደገና ማስባሰብ የቻሉት ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር ተድባበ ማርያምን እንደ ዋና ከተማቸው አድርገው ነው።

በመጨረሻም አፄ ገላውዴዎስ እግዚአብሔር አምላክ ግራኝ አሕመድን ድል እንዲያደርግላቸው በጾምና በጸሎት ተወስነው እግዚአብሔርን እየተማፀኑ ቆይተው ከሞትና ከምርኮ የተረፈ ጦራቸውን አስባስበውና የጦር ዝግጅት ድርገው አሕመድ ግራኝ ይገኝበታል ወደተባለበት አካባቢ ዘመቻ አድረገዋል። ሲዘምቱም በዐፄ ዳዊት (ቀዳማዊ) ዘመነ መንግሥት ከቅድስት ሀገር ኢየሩሣሌም እንደመጣች የሚነገርላት ታቦተ ልደታ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ተድባበ ማርያም አስቀምጠዋት ትኖር ስለነበረ በአማላጅነቷ እንደምትረዳቸው በመተማመን አብራቸው እንድትዘምት አድረገዋል። በዘመቻ ወቅት እንደ መንብር አድርገው ታቦተ ልደታን ያሰርፉበት የነበረው መንበር እስከ አሁን ድረስ የዘመቻ መንበር እየተባለ ቤተ መቅደስ ውሰጥ ይገኛል። በየዓመቱ ጥምቀተ ባሕር ሲወረድ እንደ መንበረ ሁኖ የሚያገለግለው ይህው ታሪካዊ መንበር ነው።

በአማላጅነቷ አምነው ታቦተ ልደታን ይዘው የዘመቱት አፄ ገላውዴዎስ ግራኝን ገጥመው ደንቢያ ፎገራ ውስጥ ልዩ ስሙ ዘንተራ ከተባለ ቦታ ላይ በእመቤታችን ኃይል የካቲት ፲፮ (16) ቀን ፲፭፻፴፭ (1535) ዓ ም ድል አድርገውታል። ዜና ገላውዴዎስ የተባለው መጽሐፍ አፄ ገላውዴዎስ በየካቲት ወር ግራኝን ድል ካደረጉ በኋላ በሚያዝያ ወር ተድባበ ማርያም እንደ ገቡ ነው የዘገበው። አፄ ገላውዴዎስ ተድባበ ማርያም



Scanned by CamScanner

ገብተው በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብርሃ ወአጽብሐ ሠርተውት የነበረው ሥርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አድርገዋል፤ እራሳቸውም ብዙ ሥርዓት ሠርተዋል። ለምሳሌ፡-ከአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት (330 ዓ ም) ጀምሮ ጥር 21 ቀን (የጥር ማርያም) ሲከበር የነበረውን ዓመታዊ ክብረ በዐል ከጥር 21 ቀን፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት በዐል ታስቦ ወደ ሚውልበት ግንቦት አንድ ቀን በማዛወር ግንቦት አንድ ቀን (የግንቦት ልደታ) እንዲሆን አድረገው የድል በዐላቸውንም ከእመቤታችን የልደት በዐል ጋር ግንቦት አንደ ቀን በታላቅ ድመቀት አክብረዋል። በበዐሉም ላይ በአሥራ አምስት ዓመቱ የጦርነት ዘመን ችግር ውስጥ ለነበረችው ኢትዮጵያና የችግሩ ገፈት ቀማሽ ለነበሩት ሕዝበ ክረስቲያን በሙሉ ጦርነቱ በድል መጠናቀቁን አብሥረዋል። በመቀጠልም "ተድባበ ማርያም ንግሥት ሠይፈ ገላውዴዎስ፣ የግራኝ እመቤት፣ አፈወ ድንግል በትረ ያርክ" ብለው በአዋጅ አፅንተዋል። እዚህ ላይ ነጉሡ በዓዋጅ ካፀኑዋቸው ውሣኔዎች መካከል፡-

ሀ. ተድባበ ማርያም ንግሥት ሠይፈ ገላውዴዎስ፣

ለ. የግራኝ እመቤት እና

ሐ. አፈወ ድንግል በተረ ያርክ፣ የሚሉት የንጉሡ አዋጆች በየራሳቸው ልዩ ልዩ ትርጓሜ አላቸው።

ሀ. ተድባበ ማርያም ንግሥት ሠይፈ ገላውዴዎስ፡-

አፄ ገላውዴዎስ ተድባበ ማርያም ንግሥት ብለው በአዋጅ ማወጅ ብቻ ሳይሆን ለተድባበ ማርያም ቤተ ክረስቲያን ሢሶ መንግሥታቸውን ሰጥተው በቤተ መንግሥታቸው ሁሉ ልዩ ክብር እንዲኖራት አድረገዋል። የህንን የንጉሡን አዋጅ የሚያጠናክረው ከአማራ ሣይንት በቅርብ እርቀት የሚገኘው የዳውንትና የጋይንት ሕዝብ ነው። የዳውንትና የጋይንት ሕዝቦች ተድባበ ማርያምን ንግሥት



Scanned by CamScanner

እያሉ ነው የሚጠሯት ለምሳሌ፦ ተድባበ ማርያም ሂደን መጣን ለማለት ንግሥት ሂደን ተሳልመን መጣን ነው የሚሉት ይህም ከአፄ ገላውዴዎስ አዋጅ ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ስያሜ እንጂ ሕዝበ ክርስቲያኑ ዝም ብሎ የፈጠረው ስያሜ አይደለም፡፡

ለ. የግራኝ እመቤት፦

አፄ ገላውዴዎስ ከተድባበ ማርያም የልደታን ፅሌ ይዘው ዘምተው ግራኝን ድል በማድረጋቸው ድሉ የእመቤታችን እንጂ የኔ አይደለም ሲሉ እራሳቸው ንጉሡ ይግራኝ እመቤት ብለዋታል። በመላ ኢትዮጵያ ያሉ አብያተ ክርስቲናትን ሲያቃጥልና ሲያጠፋ ወዶ ሳይሆን ተገዶም ቢሆን ያላዋረዳት፣ ምንም አይነት ጥፋት ያላደረሰባት ለማለት የተጠቀሙት ኃይለ ቃል ነው እንጂ በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት የማያመንና ሕዝበ ክርስቲያንን በግፍ ሲገድልና አብተ ክርስቲያናትን ሢቃጥል የነበረ በዚያው በአረመኔነቱ እንደፀና የተገደለው ግራኝ አሕመድ እመቤቴ ብሎ ተንበርክኮላታል ለማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ሳይወድ በግድ እንደ ሚገዛ እንደ ክፉ አገልጋይ አንበርክካዋለች፣ በወዳጇ በአፄ ገላውዴዎስ አድራ የኢትዮጵያ ጠላት የነበረውን ግራኝ አሕመድን አጥፍታላቸዋለችና በተድባበ ማርያም ኃይል እንጂ በእኔ ኃይል አልጠፋም ለማለት ግራኝን ድል ያደረኩበት ኃይሉም ጉልበቱም የተድባበ ማርያም ነው ሲሉ ተድባበ ማርያምን የግራኝ እመቤት ብለዋታል፡፡ ከአፄ ገላውዴዎስ አዋጅ በመነሣት የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን የግራኝ እመቤትን! እያለ ይምልባታል፡፡ ከዚህ በመነሣት የዚህን ጽሑፍ አዘጋጅ ጨምሮ ተድባበ ማርያም አካባቢ ተወልደው ያደጉ ሁሉ የግራኝ አመቤትን! ሲሉ መስማት የተለመደ ነው፡፡

ሐ. አፈወ ድንግል በትረ ያርክ፦

አባ አፈወ ድንግል የተባሉት ሊቅ መነኩሴ ከግራኝ አሕመድ ጋር በተደረገው ጦርነት በፊት ከአፄ ልብነ ድንግል ጋር በኋላም ከአፄ



Scanned by CamScanner

ገላውዴዎስ ጋር በመሆን የተዋጉና ያዋጉ አርበኛ መነኩሴ ናቸው። ስለሆነም አፄ ገላውዴዎስ ከድል በኋላ ሊቅነትን ከመንፈሳዊነት ጋር አስተባብረው የያዙትን አባ አፈወ ድንግልን በትረ ያርክ አፈወ ድንግል ብለው የተድባበ ማርያም በትረ ያርክ አድርገው መሾማቸውንና የበትረ ያርኩን ሹመት በአዋጅ ማፅናታቸውን ለማስረዳት ነው። ሌላው አፄ ገላውዴዎስ ተድበበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሠሩት ልዩ ሥርዓት ሥረዓት ደወል ወይም የደወል ሥርዓት ነው። ይህውም፡- በርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ጊዜም ሆነ ደወል በሚደወልበት በማንኛውም ሰዐት ቃጭል ከቀርን ጋር እንጂ እንደ ሌሎች ገዳማትና አድባራት እንዲሁም ካቴድራሎች ቃጭል ብቻውን አየደወልም። ምክንያቱም ንጉሥ ገላውዴዎስ ተድባበ ማርያም ሁል ጊዜም ደወል ሲደወል ሁለት ቃጭሎች ከነጋሪት (ከከበሮ) ጋር አብሮ እንዲመታ የሚል ሥረዓት ሠርተው በአዋጅ አፅንተዋል። ይህም ሥርዐት እስከ አሁን ፀንቶ በተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከሰሙነ ሕማማት ውጪ ባሉ ዕለታት ሥርዓተ ደወል የሚፈጸመው ቃጭል ከከበሮ ጋር በመምታት ነው እንጂ እንደ ሌሎች ገዳማትና አድባራት የቃጭል ደወል ብቻውን አይደወልም። ተድባበ ማርያም ቃጭል ብቻውን የሚመታው በሰሙነ ሕማማት ብቻ ነው።

## ምዕራፍ አራት

## ከትምህርት መንገድ ፈቀቅ የሚል ሰው በሙታን ጉባኤ ይቀመጣል! ምሳ፡- 21፤16

የአብነት ት/ቤት ታሪካዊ አመጣጥና የተጀመረበት ዘመን ረዥም ዘመናት ያስቆጠረ መሆኑ ይታወቃል። በተለይም ደቀ መዛሙርት በመሰብሰብና ጉባዔ በመዘርጋት ትምህርት መስጠት የተጀመረው በብሉይ ኪዳን ዘመን መሆኑን ታላቁ መጽሐፍ ቅዱሳችን ያስረዳል።



Scanned by CamScanner

በዚያን ዘመን የተጀመረው የመንፈሳዊው ትምህርት ቤት እስከ ሐድስ ኪዳን ደርሷል።በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 120 ቤተ ሰብ (ደቀ መዛሙርትን) መሥርቶ ለሦስት ዓመታት ከሦሰት ወር አንድነቱን፤ሦስትነቱን አስተምሮ ሒዳችሁ አስተምሩ ብሎ ወደ ዓሐም እንደ ላካቸው ቅዱስ ቃሉ ይነግረናል።

ቅዱሳን አበው ሐዋርያትም ከጌታ በተማሩትና እንዲያስተምሩ በታዘዙት መሠረት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ዙረው አስተምረዋል። ከሐዋርያት በመቀጠልም እንደ ተፍጻሜ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ያሉ ሊቃውንት እንዳስተማሩና ለቤተ ክርስቲያን የማያልፍ ሥራ ሠርተው እንዳለፉ የቤተክርስቲያናችን ታሪክ ያስረዳል።

እንደ ዘመኑ የታሪክ ተመራማሪዎች እምነት በአገራችን ኢትዮጵያም ትምህርት መሰጠት የተጀመረው ከዛሬ ሰባት ሺህ /7000/ ዓመታት በፊት በዳዓማት ዘመነ መንግሥት እንደ ሆነ መምህር ከህሳይ ገብረ እግዚአብሔር ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 30 ላይ ጠቅሰውታል። ከዚያም ከቀዳማዊ ምንይልክ ዘመን 982 ቅልክ ጀምሮ በሕገ ኦሪት ሲተዳደሩና መስዋዕተ ኦሪት ሲሰዋባቸው በነበሩ ጥንታውያን አድባራት ወቅቱና ጊዜው በሚፈቅደው መሠረት ትምህርት ይሰጥባቸው እንደ ነበረ በቃልና በጽሑፍ እየተተረከ ከዘመናችን የደረሰውና ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረው ታሪካችን ሕያው ምስክር ነው።

በዚህ መሠረት ሥርዓተ ትምህርት ቀርፀው ሲያስተምሩ ከነበሩ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት መካከል አክሱም ጽዮን፣ ተድባበ ማርያም፣ መርጡለ ማረያም፣ ጣና ቂርቆስ፣ ደብረ ዳሞ፣ ደብረ እግዚአብሔር ወይም በአሁኑ ስሙ ሐይቅ አባ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም፣ ደብረ ሃዘሎ እና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው።



Scanned by CamScanner

በኋላም የተስዓቱ ቅዱሳንን ወደ ሀገራችን መምጣት ተከትሎ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በአክሱም፣ በጣና፣ በጽርሐ አርያም ዙር አምባ እና በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች ተንቀሳቅሶ በማስተማሩ ጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት እያደገና እየሰፋ መጥቶና አድማሱን አሰፍቶ በመላው ኢትዮጵያ ለመዳረስ በቅቷል።

በመቀጠልም አባ ኢየሱስ ሞዐ፣ አባ ጊወርጊስ ዘጋስጫ በደበረ እግዚአብሔር (ሐይቅ)፣ አባ በጸሎተ ሚካኤል በደብረ ጎል፣ አዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል በተድባበ ማርያም፣ ዮሐንስ ገብላዊና ሌሎችም አበው መምህራን ጉባኤ ቤቶች በመላ ሀገራችን እንዲፋፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ከነዚህ ለጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት መካከል በ982 ዓመተ ዓለም ቅልክ፣ በአፄ ምንይልክ ዘመነ መንግሥት በሊቀ ካህናቱ አዛርያስና በመሥፍኑ ሣቤቅ የተመሠረተችው ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም በግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት።

በርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም የአዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የድጓ ምስክር ት/ቤት፣ የካህናት ማሰልጠኛና አጠቃላይ የአብነት ት/ቤት አላማም እንደ ቀድሞው ሁሉ ዛሬም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቂ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት በማሳደግ ለቤተ ክርስቲያናችን ብሎም ለአገራችን የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ነው።

በመሠረቱ የአዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የድጓ ምስክር ት/ቤት፣ የካህናት መሰልጠኛና የአብነት ትምህርት ቤት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ አሁን የተጀመረ ሳይሆን ታሪክ በአምዱ የሚያስታውሳቸው አባ ጌራና አዛዥ ራጉኤል ቅዱስ ያሬድ ለደረሰው ዜማ ምልክት ያዘጋጁበት በዕድሜ አንጋፋ የሆነ መንፈሳዊ ተቋም



Scanned by CamScanner

ነው። ይህ መንፈሳዊ ተቋም እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና ሌሎችም ቅዱሳን ሊቃውንትን ያፈራ አንጋፋና ዕድሜ ጠገብ ተቋም ነው።

ነገር ግን ጉባዔ ቤቱን ቀድሞ በኢኮኖሚ ይደግፉ የነበሩ ምእመናን ድጋፋቸው እየቀነሰ በመምጣቱና የአብነት መምህራንና ተማሪዎች የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ለፍልሰት በመዳረጋቸው ጉባዔ ቤቱ በመዳከም ላይ ይገኛል። ከቤተ ከህነቱም የተጣከለ አሰራር ያለመኖርና ትኩረት የማጣት፣ የዘመኑ ሁኔታም በልመናና በጊዜያዊ ዕርዳታ ህልውናውን ይዞ መቀጠል የማይፈቅድ መሆኑ፣ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሁኖበታል።

እንደ አማራ ሣይንት ወረዳም ሆነ እንደ አጠቃላይ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከተው ወደ አብነት ት/ቤቶች እየገቡ ካሉት ተማሪዎች መካከል በቁጥር ቀላል የማይባሉ አላማቸውን እስከ ግቡ ለማድረስ ተስኗቸው ይታያል። በእነዚህና መሰል ችግሮች ምክንያት ጥንካሪያቸው እየተዳከመ ተስፋቸው እየጨለመ መምጣታቸውና ከአካባቢ ለቀው እንደ ሚሄዱ በዚሁ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች አመልካች ናቸው።

በተለይ በአማራ ሣይንት የቀሩትንም ለማጥፋት አጅባርን ማዕከል አድርገን አምሐራ ሳይንትን እናሰልማለን በሚሉ ዘመን የፈጠራቸው አክራሪ ሙስሊሞችና ተሐድሶ/መናፍቃን/ አፀራረ ቤተ ክርስቲያን የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ ደፋ ቀና እያሉ በመሆኑ እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለመቀነስ ብሎም በሂደት ለመከላከል በአሁኑ ወቅት በጣም ተቀባይነት ያለውና ለቤተ ክርስቲያን በሚሰጠው ጠቃሜታ ተወዳዳሪ የሌለው አብነት ት/ቤቶችን መጠናከር መተኪያ የሌለው ተግባር ነው። ስለ ሆነም የርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽ/ ቤት ነባሩንና አንጋፋውን የአባ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የድጓ ምስክር ት/ቤት፣ የካህናት ማሰልጠኛና የአብነት ትምህርት ቤት ለመገንባት ፕሮጀክት ቀርፆና ከ5000 ካ.ሜ በላይ



Scanned by CamScanner

መሬት ከመንግሥት አስፈቅዶ እና ተርክግንባታውን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል። ለጉባዔ ቤቱ ግንባታም ቅድሚያ በመስጠት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የመሠረት ደንጊያ በማስቀመጥ የግንባታ ሥራው በፍጥነት እንዲጀመር የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል። ነገር ግን ለግንባታውን በተያዘለት ጊዜ ሠርቶ ማጣናቀቅ በደብሩ ሰበካ ጉባዔ አቅም ይሚቻል ባለመሆኑ በጎ አድራጊ ምእመናንን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

የአምሐራ ሳይንት ወረዳ በውስጧ ጥንታዊት፣ ታሪካዊት፣ ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያምን ጨምሮ በወረዳው ቤተ-ክህነት ሥር 14(አሥራ አራት) ገዳማት 40 (ዓርባ) አድባራትና ሌሎች ከ110 በላይ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት፣ በአጠቃላይ ከ165 በላይ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙባት ወረዳ ናት፡፡ እንዲሁም ከ200,000 በላይ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚኖር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 95.5 ፐርሰንት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ነው፡፡

አምሐራ ሳይንት ወረዳ ዮሐንስ ገብላዊ የተባለ የዋድላ ድላንታ ተወላጅ ሊቅ ቅኔን ፈልስፎ የመጻሐፍትን ምስጢራት በሰምና ወርቅ እያስማማ ከስድ ጽሁፍ ይልቅ በግጥም መልክ እንደ ደረሰበት የሚነገርለት ታላቁ የታቦር ተራራ መገኛም ናት። አጤ ይኩኖ አምላክ የነገሠበት ታላቁ የታቦር ተራራ ከተድባበ ማርያም በቅርብ ርቀት ነው የሚገኘው። ይህንንም ተከትሎ ተድባበ ማርያም የቅኔ ሙያ፣ የአማርኛ ቋንቋ እና የዜማ ምልክት የተደረሰባት የስልጣኔ ምንጭ ናት። በአማራ ሣይንት ወረዳ በየአድባራቱና ገዳማቱ በርካታ የአብነት ት/ቤቶች ቢኖሩም በአሁኑ ወቅት ግን ከርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድርባበ ማርያም ውጭ ያሉት የአብነት ት/ቤቶች ሁሉ ተዘግተዋል ማለት ይቻላል፡፡



Scanned by CamScanner

ለዚህም ዋናው ምክንያት አሁን ባለው ሥርዓተ መንግሥት ለዘመናዊ ትምህርት በተሰጠው ትልቅ ትኩረት ኅብረተ ሰቡ ልጁን ወደ ዓለማዊ ትምህርት በመስደዱና እንደ በፊቱ በእንተ ስማ ለማርያም ብሎ ለሚለምን የአብነት ተማሪ የሚያለምን በመጥፋቱ እና የሚያስተምሩ መምህራን ወንበራቸውን በማጠፍ የዕለት ጉርስ የሚያገኙበትን አማራጭ በመፈለጋቸው ነው።

በመሆኑም በወረዳዋ በርካታ አብያተ ክርትያናት እና የእምነቱ ተከታዮች ከአገልግሎት ውጭ እየሆኑ በመምጣታቸው ይህንን የአብነት ት/ቤት በመገንባትና በማጠናከር የወረዳውን የኋላ ታሪክ መመለስ ለነገ የማይተው ይልቁንም ለታሪኩና ለሃይማኖቱ ተቆርቋሪ የሆነ ኢትዮጵዊ ሁሉ ሊረባረብበት ይገባል።

ፕሮጀክቱ በዋናነት ዓላማ አድርጎ የተነሣው ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት አካባቢ ያሉትን የአብነት መምህራንና ተማሪዎችን በተናጠል ተስፋ እያስቆረጡ ያሉ ችግሮችን ማዕከላዊ በሆነ መልኩ መፍታትና ተስፋ በተሞላበት ሁኔታ የመማር ማስተመሩን ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ ነው። ተያያዥ ዝርዝር ዓላማዎችም ያሉት ሲሆን ለመንፈሳዊ አስተምሮቶች እረዳት በሆኑ ቁሳቁሶች የተደራጁና ዓላማቸውን የሚያውቁ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ራዕይ ሰንቀው የሚማሩ ተማሪዎችን ሊያስተምር የሚችል ሞዴል (ምሳሌ) የአብነት ትምህርት ቤት ማድረግ ነው።

በርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የአባ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የድጓ ምስክር ት/ቤት፣የካህናት ማሰልጠኛና አጠቃላይ የአብነት ት/ቤት ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ ለፕሮጀክቱ ያስፈልገዋል ተብሎ በባለ ሙያዎች የተጠናው ጠቅላላ ወጪ ብር ከ10,000,000. (አሥር ሚሊዬን ብር) በላይ ነው።



Scanned by CamScanner

የፕሮጀክቱ ወጪ ይገኛል ተብሎ የታሰበውም ለሃይማኖታቸው፣ ለታሪካቸውና ለሀገራቸው ቀናእያን ከሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሚገኝ እርዳታእና የቤተ-ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆችና ለሀገር ተቆርቋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን፣ ከበጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች ነው፡፡

ስለዚህ በሀገር ወስጥና በውጪ ያላቸሁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለዚህ ታሪካዊና ጠንታዊ ት/ ቤት ግንባታና ለአብነት ትምህርት ቤቱ ግንባታ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ በአይነትና በገንዘብ በመደገፍ ሃይማኖታዊና ሀገራዊ ኃላፊነታችሁን ትወጡ ዘንድ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ተድባበ ማርያም ስም እንጠይቃለን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም እና ዘመን ተሻጋሪ ቅርሶቿ

ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አያሌ የታሪክ መዘክሮች፣ መንፈሳዊና ባህላዊ ቅርሶች የሚገኙባት ጥንታዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በዚህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት ቅርሶች መካከል አንዳንዶቹ በተቀሩት የአገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ይቅርና በሌላውም ዓለም የማይገኙ፤በጣም ውሱን የሆኑ፤እጅግ ጥንታውያንና ታሪካውያን መሆናቸው በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት፡ ከፍተኛ ባለሙያዎች፡-

1ኛ. በ1985 ዓ.ም፣

2ኛ. በ2002 ዓ.ም ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ ቅርሶቹ በአግባቡ ለምተውና ተጠብቀው ከአገር ውስጥና ከውጭ ጎብኝዎች ተገቢውን



Scanned by CamScanner

ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያስገኙ ለማድረግ ትኩረት ሳይሰጣቸው በተጣበበ ዕቃ ቤት ውስጥ በመደራረብና በመከማቸት ለብልሽት፣ለጉስቁልና እና ለሌሎች አደጋዎች በተጋለጠ መልክ ተቀምጠው ይኖሩ ነበር። ይሁን እንጂ የአማራ ብሔራዊ፣ ክልላዊ መንግሥት ከአማራ ሣይንት ወረዳ መሥተዳድር እና ከደብሩ ሰበካ ጉባዔ ጋር በመተባበር በከፍተኛ ወጪ ያስሠራው ዘመናዊ ሙዚዬም ሥራ በመጀመሩ በቅርሶቹ አቀማመጥ ላይ የነበው ስጋት ከሞላ ጎደል ተቀርፏል፡፡

ርዕሰ አድባራት ወገዳማት ተድባበ ማርያም በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ድርሻ ያላትና ብርካታ የቅርስ ክምችት ያለባት ቤተ ክርስቲያን ናትና፣ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ከሚገኙት ዋና ዋና ተንቀሳቃሽታታሪካዊ ቅርሶች ወስጥ፡-ጥን ታውያን፣ከጽርዕና ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጎሙና አሁንም ድረስ የነዚህ ቋንቋዎች አሻራ ያለባቸው ብዙ ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

ሀ. በደብሯ ውስጥ ከሚገኙት ቅዱሳትመጻሕፍት መካከል፡-

- ገድለ አዳም፣
- በዓረብኛና በግዕዝ የተጻፈ ወንጌል፣
- ወንጌለ ወርቅ (የወርቅ ጉብጉብታያለበት ወንጌል)፣
- አብርሃ ወአጽብሐ የነፁትን የተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲባርኩና፣
- ቅዳሴ ቤቱን ሲያከብሩ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የቀደሱበት በአረማይካ የተጻፈ በየትኛውም አካባቢ የማይገኝ ጥንታዊ የገበታ ቅዳሴ መጽሐፍና፣
- ከሣቴ ብረሃን አቡነ ሰላማ የቀደሱበት መጽሐፈቅዳሴ ተጠቃሾች ናቸው፡፡



Scanned by CamScanner

ለ. ከጥንታውያን ሥዕሎች ውስጥ:-

- የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማማት ታሪክ የያዘ የብራና ሉህ ሥዕል፣
- ቅዱስ ሉቃስ የሳላት ሥዕለ አድኅኖ ምስለ ፍቁር ወልዳ፣
- ሥዕለ እግዚአብሔር አብ እና ሌሎች የእመቤታችን፣
- የሰማዕታትናየመላእክትሥዕሎች።

ሐ. ከከበሩ መስቀሎች ውስጥ:-

- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር እያለ በምሣሌ ያስተማረበትና የሰበከበት ነዋ በግዑ መስቀል፣
- አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የቀደሱበት የእጅ መስቀል፣
- የዕጨጌ ዮሐንስ በትረ ሆሳዕና የእጅ መስቀል፣
- የአቡነ አኖሪዎስእየእጅ መስቀል፣
- የአቡነ ቄርሎስ እየእጅ መስቀል (አቡነ ቄርሎስ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዲቆና የሰጡ ግብፃዊ ጳጳስ ነቸው) እና ሌሎች ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስና ከእንጨት የተሠሩ የተለያዩ ጥንታዊ የመጾርና የእጅ መስቀሎች።

መ. ከክብር አልባሳትና ከወግ ዕቃዎች ውስጥ:-

- የነገሥታት ልብሰ መንግሥት፤
- የራስ የደጃዝማቾች የክብርና የማዕረግ አልባሳት፤
- የወርቅና የብር ጉብጉብታ ያለባቸው ድባቦችና በወርቀና በብር የተንቆጠቆጡ የነገሥታ ጃንጥላዎች፤
- ከወርቅና ከአልማዝ የተሠራ ዘውድ፤ ወርቅ ቅብ የነሐስና የብር ዘውዶችና አክሊሎች፤
- ከንጨትና ከአሣ ነባሪ የተሠራ መንበረ ዳዊት፤
- ባለ ወርቅ ጣፋ ጋሻ፤ባለብር ጉብጉታ ጋሻና ጦሮች፤



Scanned by CamScanner

• ሳበው የሚባለው በአፄ ገላውዴዎስ የተበረከተ ጠሞንጃ እና ሌሎች የጦር መሣሪያወች፤

• 700 ዓመትእዕድሜ ያስቀጠረ ድርብ ክፍል ያለው ግዙፍ ጎደ ድንኳን፡፡

ሠ. ከከበሩ የሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ቅርሶች ውስጥ፡-

• ሔሮድስ ያስየጨፈጨፋቸው ሕፃናት አጽምና የቅዱስ ጊዮርጊስን ጨምሮ የ28 ሰማዕታት አፅመ ቅዱሳን፤

• ሥዕርተ ሐና፣ እመ እግዝእትነ ማርያም

• ሠለስቱ ምዕት የጸለዩበት እና አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ከእስክንድርያ አምጥተው ከፐትርክናው ጋር ተድባበ ማርያም ያስቀመጡት ዘይቄድስ ኩሎ የተባበለለት ቅብዐ ሜሮን፤

ረ. በተድባበ ማርያም ከሚገኙ መቃብረ ነገሥት መካከል፡-

• የአፄ ገላውዴወስ፣

• የአፄ ይስሐቅ፣

• የአፄ ቴዎድሮስ ቀዳማዊ፣

• የአፄ እስክንድር፡

• የአፄ ሚናስና የአፄ ሠርፀ ድንግል፣

• እንዲሁም የጎንደርና የሸዋ አማራዎች አባት በመባል የሚታወቀው የጸሐፌ ላሕም ብሥራተ ሚካኤል፣

• ዕጬጌ ዮሐንስና የሌሎች ነገሥታት አጽም፣ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነዚህ ብርቅና ድንቅ የሆኑ ቅርሶች ለዘመናት ከዘራፊዎችናእእንደ እሳት አደጋ ካሉት ጉዳቶች ሲጠበቁ የኖሩት ከአካባቢው ኅብረተ ሰብ ውስጥ በርሰተ ጉልት ሥሪት በተመደቡና ጥራን (ትሩራን) በሚል ስያሜ በሚታወቁ አሥራ ሁለት (12) መደበኛ ጠባቂዎች ነበር፡፡ ይህ የጥበቃ ዘዴ የተዋቀረው ደብሯ የተመሠረተችበት ቦታ ዙሪያውን



Scanned by CamScanner

በተፈጥሮ ገደል የታጠረና ወደ አምባው ለመግባትና ለመውጣት የሚቻለው በ12ቱ በሮች አማካኝነት ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም 12ቱ ጥራኖች እያንዳንዳቸው አንድ አንድ በር የመጠበቅ ኀላፊነት ተሰጥቷቸው እነሱም በአካባቢውና እስከ ዋሮ ድረስ በሚመደቡት ዘበኞች እየታገዙ የቅርስ ክምችት ካለበት ከደብሩ ዕቃ ቤት አንስቶ እስከ መውጫና መግቢያ በሮቹ ድረስ የቅርስ ዘራፊዎችን በመከላከል ላይ ባነጣጠረ የጥበቃ ዘዴ የደብሩን ክብርና ንብረት ሲያስጠብቁና ሲያስከብሩ ኑረዋል፡፡ዕቃ ቤቱን የሚጠብቁት መጋቢም ከበትረ ያርኩ ቀጥሎ ተጠሪነታቸው ለነዚህ ጥራን (ጥሩርን) በመባል ለሚታወቁት ባላባቶች ነው፡፡



Scanned by CamScanner



Scanned by CamScanner